# ስለ ሄፐታይተስ ቢ ምርመራ እና ክትባት ምን ማወቅ ያስፈልገኛል?

## ዋና ዋና ነጥቦች

- ሄፐታይተስ ቢ በቫይረስ የሚመጣ የጉበት በሽታ ነው ፡፡
- የሄፐታይተስ ቢ ምልክቶች እንደ ድካም ፣ ተቅማጥ ፣ ማስመለስ እና ሌሎችም ይገኙበታል ፡፡
- ደህንነቱ የተጠበቀ የግብረ-ስጋ ግንኙነትን በማድረግ እና የግል ምርቶችን ባለመጋራት ሄፐታይተስ ቢን ይከላከሉ፡፡
- ሄፐታይተስ ቢ ካለብዎ በየ 6-12 ወሩ ዶክተርዎን ይጎብኙ ፡፡

1. **ሄፐታይተስ ቢ ምንድን ነው?**

ሄፐታይተስ ቢ በሄፐታይተስ ቢ ቫይረስ ፣ በጀርም ምክንያት የሚመጣ የጉበት በሽታ ነው ፡፡ በሰውነት ውስጥ ረዘም ላለ ጊዜ ሊቆይ እና ለሞት ሊዳርጉ የሚችሉ እንደ የጉበት ጉዳት እና ካንሰር ያሉ መጥፎ የጤና ችግሮች ያስከትላል ፡፡

2. **በሄፐታይተስ ቢ እንዴት ሊያዙ ይችላሉ?**

ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ እና መርፌዎችን / ምላጭዎችን መጋራት ጨምሮ የታመመ ሰው ደም ወይም የሰውነት ፈሳሽ ወደ ሰውነትዎ ሲገባ በሄፐታይተስ ቢ ሊያዙ ይችላሉ፡፡

እናቲቱ ይህ ጀርም ካለባት ህፃናት በሚወልዱበት ጊዜ በበሽታው ሊያዙ ይችላሉ ፡፡

3. **የሄፐታይተስ ቢ ምልክቶች ምንድ ናቸው?**

በሄፐታይተስ ቢ የተያዙ ብዙ ሰዎች ህመም አይሰማቸውም ወይም ለብዙ ዓመታት ምልክቶች ላይታዩባቸው ይችላል ፡፡ ነገር ግን ምልክትቶች የሚያካትቱት

- ድካም
- ተቅማጥ
- ማስመለስ ፣ ጃዉንዳይስ (ወደ ቢጫ የሚያደላ የቆዳ ወይም የአይን ቀለም)
- በጡንቻዎች ፣ በመገጣጠሚያዎች እና በሆድ ውስጥ ያለ ህመም ፡፡

ምልክቶች ባይኖሩብዎትም እንኳ ሄፐታይተስ ቢ ኢንፌክሽን አሁንም የከፉ የጤና ችግሮች ሊያስከትል ይችላል ፡፡ አንድ ሰው በሽታው እንዳለበት ለማወቅ የደም ምርመራ ያስፈልጋል ፡፡

## በ IOM ወደ አሜሪካ ለሚጓዙ ስደተኞች የሚደረግ የሄፐታይተስ ቢ ምርመራ እና ክትባት

- IOM እንደ ስደተኛ ወደ አሜሪካ ከመምጣትዎ በፊት ደምዎን አንድ ጊዜም እንኳ ቢሆን መርምሮ ሊሆን ይችላል ፡፡
- በአሜሪካ ውስጥ ያለው ዶክተርዎ ያን ጠቃሚ የጤና መረጃ እርስዎን ለመንከባከብ ይጠቀምበታል።
- በሄፐታይተስ ቢ ካልተያዙ IOM በበሽታው እንዳይያዙ የሚከላከል እስከ 3 ክትባት / ሾትስ ሊሰጥዎት ይችላል ፡፡
- በአሜሪካ ውስጥ ያለው ዶክተርዎ በሽታውን ለመከላከል የሚያስፈልጉዎትን ሁሉንም ክትባቶች (ሾትስ) መውሰድዎን ያረጋግጣል ፡፡

## ሄፐታይተስ ቢ ካለብዎ ዶክተርዎ የሚያደርገው፡

- ስለ ሄፐታይተስ ቢ ያስተምረዎታል እንዲሁም ጤናማ እንዲሆኑ ተጨማሪ የሕክምና ምርመራዎችን ይመክራል ፡፡
- ሁሉም የቤተሰብዎ አባላት እና / ወይም የወሲብ አጋሮችዎ እንዲሁ የሄፐታይተስ ቢ ምርመራ እንዲያደርጉ ይመክራሉ ፣ እነሱም ነገቲቭ ከሆኑ የሄፐታይተስ ቢ ክትባት / መርፌ ይወስዳሉ ፡፡
- በሄፐታይተስ ቢ የተጠቁ ነፍሰ ጡር ሴቶች ሕፃናት በተወለዱበት ቀን የሄፐታይተስ ቢ ክትባት እንዲወስዱ ይመክራል ፡፡

- ሄፐታይተስ ቢን አስመልክቶ በሕይወት ዘመንዎ ሁሉ በየ 6 ወሩ ሐኪም እንዲያገኙ መጠየቅ ወይም ጊዜ ማመቻቸት - ምንም እንኳን መደበኛ ስሜት ቢሰማዎትም ፡፡

## ሄፐታይተስ ቢ ካለብኝ ሌላ ምን ማድረግ አለብኝ?

**የሄፐታይተስ ቢ ተህዋሲያንን ለማከም አብዛኛውን ጊዜ በየ 6-12 ወሩ ሐኪምዎን ያነጋግሩ ፡፡**

- የጥርስ ብሩሾችን ፣ ምላጭዎችን ፣ የጥፍር መቁረጫዎችን ፣ ወረንጦ(ትዊዘርስ) ወይም መርፌዎችን አይጋሩ ፡፡
- ሁል ጊዜ ኮንዶምን ይጠቀሙ ፡፡
- አልኮል አይጠጡ ፡፡
- ቁስል ካለብዎ እርስዎን የሚከታተል ማንኛውም ሰው ጓንት ማድረግ አለበት ፡፡

**ለሄፐታይተስ ቢ መመርመር እና መከተብ ለእርስዎ እና ለሚወዷቸው ሰዎች አስፈላጊ ነው ፡፡**

**ስለ ሄፐታይተስ ቢ የበለጠ ባወቁ ቁጥር የተሻለ ይሆናል ፡፡**

CENTER OF EXCELLENCE IN NEWCOMER HEALTH MINNESOTA

This material has been approved by the Minnesota Center of Excellence in Newcomer Health. Thank you to the International Organization for Migration for donating this material for adaptation and translation.